የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፵፯
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፪ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24th Year No.47
ADDIS ABABA 29th June, 2018

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፹፯/፪ሺ፲ ዓ.ም

ለከተሞች መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ……………………..……ገጽ ፲ሺ፫፻፺፫

## Content

Proclamation No.1087/2018

International Development Association Financing Agreement for financing Urban Institutional and Infrastructure Development Program Ratification Proclamation.--………………………..Page 10393

### አዋጅቁጥር ፩ሺ፹፯/፪ሺ፲

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለከተሞች መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚውል ፩፻፳፯ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (አንድ መቶ ሃያ ሰባት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) መደበኛ ብድር እና ከስኬል-አፕ ፋሲሊቲ ክሬዲት ፪፻ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (ሁለት መቶ ሚሊዮን የአሜሪካንዶላር) የሚያስገኘውን የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል መጋቢት ፲፩ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፳፫ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

### PROCLAMATION NO. 1087/2018

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

WHEREAS, a Financing Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association shall provide to the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of $127,000,000 (One hundred twenty seven million United States Dollar) Regular Credit; and $200, 000,000 (Two hundred million United States Dollar) from Scale- Up Facility Credit for financing Urban Institutional and Infrastructure Development Program was signed in Addis Ababa on the 20th day of March, 2018;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Financing Agreement at its session held on the 31st day of May, 2018;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለከተሞች መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፹፯/፪ሺ፲" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል መጋቢት ፲፩ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረሙት የብድር ስምምነቶች ቁጥር 6196-ET (Regular Credit) እና 6197- ET (Scale Up Facility Credit) የብድር ስምምነት ፀድቀዋል፡፡

**፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ስልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፩፻፳፯ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (አንድ መቶ ሃያ ሰባት ሚሊዮን አሜሪካን ዶላር) መደበኛ ብድር እና ከስኬል-አፕ ፋሲሊቲ ክሬዲት ፪፻ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (ሁለት መቶ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፪ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም**

**ሙላቱ ተሾመ ዶ/ር**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

NOW, THERFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Financing Agreement for financing Urban Institutional and Infrastructure Development Program Ratification Proclamation No. 1087/2018".

**2. Ratification of the Agreement**

The Financing Agreement Number 6196-ET (Regular credit) and 6197-ET (Scale Up Facility Credit) signed in Addis Ababa on the 20th day of March, 2018 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

**3. Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation**

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of $127,000,000 (One hundred twenty seven million United States Dollar) Regular Credit; and $200, 000,000 (Two hundred million United States Dollar) from Scale- Up Facility Credit in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the *Federal Negarit Gazette*

**Done at Addis Ababa, this 29th day of June, 2018**

**MULATU TESHOME (Dr.)**

**PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**